





# “አንተው ነህ መሪዩ!”

(ለክቡር ዶ/ር ዐብይ አህመድ ዕለተ-መቶኛ የጠ/ሚኒስትርነት ‘ዘመን’ መታሰቢያ ትሁን!)

በሃቅ የታነጸ - እሚያድር በቃሉ፣
ባለግርማ-ሞገስ - ትህትና ሙሉ፣
አለኝታ፣ መከታ..፣ ለዜጎች መመኪያ፣
ስም ያለው፣ ክብር ያለው - ላገሬ መጠሪያ፤
ስፈልገው የኖርኩ - በሃሳብ በምናቤ፣
አንተው ነህ መሪዩ! የገባህ ከልቤ።

ኢትዮጵያ ለጸሎት - እጆቿን ዘርግታ፣
በእንባዋ ርሳ - ዘመናትን ፈጅታ፣
ያገኘችህ ዕንቁ - የእግዚአብሔር በረከት፣
የአገር ምሰሶ - የሕዝብ ጌጥና ሃብት፤
ባንተ ደስ ይበላት - ስለቷ ሰመረ፣
ወደ ፍቅር ጉዞ አዝማች ተዘመረ፤
ከፍ ብሎ ይውጣ - ይውለብለብ ሰንደቋ፣
አንድነቷም ይመር - በመደመር ቋንቋ።

ዐብይ ኢትዮጵያዊ - ረቂቅ፣ ምጡቅ..ጀግና፣
በሃሳብ ልዕልና - በመሪነት ፋና፣
ዘመን ውስጥ ተቀምጠህ - ዘመን የተሻገርክ፣
አንድነትን፣ ፍቅርን፣.. - ሰላምን የሰበክ፣
ባለራዕይ ዕሴት - ባለፍቅር ጸጋ፣
አንተው ነህ መሪዩ! ደምረኝ ካንተጋ።

ተምዘግዛጊ ጮራ፣ በብርሃን ፍጥነት፣
ተወርዋሪ ኮከብ፣ - ባራቱም ማዕዘናት፣
የላቀ ተምሳሌት - ለስኬት እመርታ፣
የሰፊው ሕዝብ ‘ሎሌ’ - ያገር ባለውለታ፣
ጎንበስ እምልልህ - “ምን ልታዘዝ?” ብዬ፣
የናት አገሬ ልጅ! - አንተው ነህ መሪዩ!

ጌታቸው አበራ
ሐምሌ 2010 ዓ/ም
(ጁላይ 2018)





